# ጥያቄና መልስ፡ በቻርተር ትምህርት ቤቶች ህግ ላይ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ያሳለፈው ውሳኔ

ከፍተኛው ፍርድ ቤት፡ የቻርተር ትምህርት ቤቶችን በተመለከተ ያሳለፈውን ውሳኔ ባለፈው ዓርብ ምሽት ላይ ይፋ ካደረገበት ግዜ ጀምሮ፡ የውሳኔውን ዝርዝራዊ ይዘትና ውሳኔው በቻርተር ትምህርት ቤቶች ( public charter school) ውስጥ በመማር ላይ ባሉት 1300 ተማሪዎች ላይ ምን ዓይነት ውጤት እንደሚያስከተል ለመረዳት ከፍተኛ ጥረት ስናካሂድ ቆይተናል።

በመሆኑም፡ ባለፉት ጥቂት ቀናት ውስጥ፡ በቤተሰቦች በኩል ሲነሱ ለቆዩት ጥያቄዎች አንዳንድ መልስ ለመስጠት እንሻለን።

**ጥያቄ፡ ከፍተኛው ፍርድ ቤት፡ የዋሽንግተን ህዝባዊ ቻርተር ትምህርት ቤቶች መመስረት፡ ህገ-መንግስታዊ ኣይደለም ብሎ የወሰነበት ምክንያት ምንድነው?**

መልስ፡ ከፍተኛው ፍርድ ቤት፡ የዋሽንግተን ህዝባዊ ቻርተር ትምህርት ቤቶች ህግ ህገ-መንግስታዊ ኣይደለም ብሎ የወሰነበት
ምክንያት ህዝባዊ የቻርተር ትምህርት ቤቶች የራሳቸውን የአስተዳደር ቦርድ ወይም ኮሚቴ ኣባላትን ስለማይመርጡ “ተራ ትምህርት ቤቶች” ወይም ህዝባዊ ትምህርት ቤቶች “common schools” (public schools) ስላልሆኑ፡ ከመንግስት የገንዘብ እርዳታ ሊሰጣቸው ኣይገባም ብሎ ከኣንድ መቶ ዓመት በፊት የተደነገገውን ህግ በመከተል ነው። ይሁንና፡ በ2012 የዋሽንግተን ድምጽ ሰጪዎች ፤ ድምጻቸውን በመስጠት የህዝባዊ ቻርተር ትምህርት ቤቶችን ህግ ኣሳልፈዋል። ይህ ህግም በመላው ኣገር ካሉት ጠንካራና ሃይለኛ ህጎች ተብለው ከሚታወቁት ህጎች መካከል አንዱ ነው። እነኚሁ ህዝባዊ ቻርተር ትምህርት ቤቶች፡ በመንግስት ከሚተዳደሩት ትምህርት ቤቶች እኩል ከፍተኛ የትምህርት ደረጃና ከፍተኛ ቁጥጥር የሚያደርጉ ትምህርት ቤቶች ናቸው። በተጨማሪም፡ የእያንዳንዱን ተማሪ የትምህርት ኣቀባበል ችሎታን ግምት ውስጥ በማስገባት የሚሰሩ ናቸው።

የፍርድ ቤቱን ኣተረጓጎም በመጠቀም፡ የሩጫ ኣጀማመር ወይም ራኒንግ ስታርት (Running Start) በመባል የሚታወቀው ( የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የኮሌጅ ትምህርቶችን እንዲያገኙ የሚያደርግ ፕሮግራም) እና ትራይባል ኮምፓክት ትምህርትቤቶች (Tribal Compact Schools for Native students) በመባል ለኣሜሪካ ህንጾች፡ ለኣላስካና ለሃዋይ ተወላጆች ተብለው የተቋቋሙ ትምህርት ቤቶች፡ በህጋዊ መንገድ በተመረጡ የስራኣስኪያጆች ቦርድ ወይም ኮሚቴ ስለማይመሩ ያገኙት የነበረው የመንግስት የገንዘብ እርዳታ ወይም ድጎማ ከእንግዲህ ወዲህ ይቋረጣል።

በግልጽ ኣነጋገር፡ ፍርድ ቤቱ ያሳለፈው ውሳኔ፡ የቻርተር ትምህርት ቤቶቹን ጥቅም፡ ጥራት ወይም ብቃት ግምት ውስጥ ሳያስገባ ነው።

ስለክሱና ( lawsuit) ስለ ውሳኔው (ruling) በበለጠ ለመረዳት እነኚህን ዌብሳይቶች ተመልከቱ።

**ጥያቄ፡ ትምህርት ቤቶቹ እንደሚዘጉ ለራሳቸው ለትምህርት ቤቶቹ በይፋ ተነግሮኣቸዋልን?**

መልስ፡ ኣልተነገራቸውም። ምክንያቱም ውሳኔው ገና ለሚቀጥሉት 20 ቀናት በስራ ላይ ኣይተረጎምም።ራሳቸው ትምህርት ቤቶቹ፡ የዋሽንግቶን ክፍለሃገር ቻርተር ትምህርት ቤቶች ማህበር Washington State Charter Schools Association (WA Charters) (ደብሊው ኤ ቻርተርስ ) እና

WASHINGTON STATE
CHARTER SCHOOLS
ASSOCIATION

ሌሎች ብዙዎች፣ ዘጠኙ የቻርተር ትምህርት ቤቶች እንዳይዘጉ የሚቻላቸውን ጥረት እያደረጉ ነው። የእያንዳንዱ ትምህርት ቤት ዋነኛ/ተቀዳሚ ዓላማ፣1300 የሚሆኑት ተማሪዎቻቸው ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉና በተማሪዎችና በቤተሰቦቻቸው ላይ ሊደርሱ የሚችሉ እንቅፋቶችን በተቻለ መጠን እንዲቀንሱ መርዳት ነው።

**ጥያቄ፣ ክፍለሃገሩ ወይም መንግስት የሚያደርገውን የገንዘብ እርዳታ ካቋረጠ፣ ትምህርትቤቶቹ እንዴት ክፍት ሆነው ሊቆዩ ይችላሉ?**

መልስ፣ የዋሽንግቶን ቻርተርስና ኣያሌ የስራ አጋሮቻችን፣ የቻርተር ትምህርት ቤቶች እንዳይዘጉና ወላጆች ልጆቻቸውን ከፍተኛ ደረጃ ባለው የህዝባዊ ቻርተር ትምህርት ቤት ውስጥ የማስገባት ምርጫቸው እንዲጠበቅ ለማድረግ፣ ያሉትን የኣጭርና የረጅም ግዚ መፍትሄዎችንና ኣማራጮችን በመዳሰስ ላይ ይገኛሉ። ግዜው ገና ነው። ሆኖም የቻርተር ትምህርት ቤቶችን በተመለከተ ኣዲስ ህግ እስከሚወጣና ኣንድ የረጅም ግዜ መፍትሄ እስኪገኝ ድረስ የገንዘብ እርዳታ ከዚህም ከዚያም እንደምናገኝ ሙሉ እምነት ኣለን።

እስከዚያው ድረስ ያሉትን ህጎችና ህጋዊ ኣማራጮችን በመዳሰስና፣ ኣገረገዢ ኢንስሊና ሌሎች ህግ ኣርቃቂዎች ይህንን በተመለከተ ልዩ ስብሰባ እንዲያደርጉና እንዲወያዩበት በመጠየቅ ላይ ነን። ድምጸን ለመስጠት እዚህ ላይ here በጣትዎ ይጫኑ።

**ጥያቄ፣ ይህ እንደሚሆን ኣስቀድማችሁ ታውቁ ኖርዋልን? ለምንድነው ስለዚሁ ጉዳይ እስከኣሁን ሳይገለጽልን ኣሁን እንድናውቅ የተደረገው?**

መልስ፣ ይህ ጉዳይ ከኣንድ ዓመት ኣካባቢ በፊት ፍርድ ቤት በቀረበበት ወቅት፣ የዋሽንግቶን ቻርተርስና (WA Charters) ሌሎች ደጋፊዎች ህጉን በመደገፍ ተከራክረዋል። ኣንዳች ውሳኔ ሊሰጥ እንደሚቻልም ኣውቀዋል። ግን የህግ ኣስከባሪዎቹ፣ ከኣሁን በፊት ለከፍተኛው ፍርድ ቤት የቀረቡ ጉዳዮችንና ፍርድ ቤቱ የሰጣቸውን ውሳኔዎች ግምት ውስጥ በማስገባት፣ እንዲህ ዓይነቱ ውሳኔ ይወሰናል የሚል ግምት ኣልነበራቸውም። ኣንዳች ዓይነት ተጻራሪ ውሳኔ እን ኳን ቢወሰን፣ ቀለል ያለና ኣጠቃላይ ህጉን የማይነካ ውሳኔ ይሆናል የሚል እምነት ነው የነበራቸው።እንዲያውም፣ ቀደም ሲል የኪንግ ክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት( King County Superior Court) የሰጠው ውሳኔ፣ ለቻርተር ትምህርት ቤቶች የሚደረገው የገንዘብ ድጎማ፣ ከሌላው ቻርተሩን ከሚመለከት ኣጠቃላይ ህግ ውጪ መታየት ይገባዋል የሚልና ኣጠቃላይ ህጉን የማይነካ ነው የነበረው። ይሄው በዋሽንግተን ድምጽ ሰጪዎች የጸደቀው የቻርተር ትምህርት ቤቶች ህግ፣ ከኣገሪቱ ህጎች ውስጥ እጅግ ጠንካራ ናቸው ከሚባሉት ህጎች ውስጥ እንደ ኣንዱ እንዲሆን ተብሎ የተረቀቀ ነው።ፍርድ ቤቱ፣ ዘጠኝ የቻርተር ትምህርት ቤቶች ከተከፈቱ በኋላ፣ ለምን እንዲህ ዓይቱን ውሳኔ ለማሳለፍ እንደፈለገ ግልጽ ኣይደለም።

**ጥያቄ፣ ይህንን ውሳኔ በተመለከተ ምን በመደረግ ላይ ነው?**

መልስ፣ የዋሽንግተን ቻርተርስ ( WA Charters)፣ራሳቸው የቻርተር ትምህርት ቤቶችና ብዙዎች ሌሎች፣ የቻርተር ትምህርት ቤቶች እንዳይዘጉና ወላጆች ልጆቻቸውን ከፍተኛ የትምህርት ደረጃ ባለው የህዝባዊ ቻርተር ትምህርት ቤት ውስጥ የማስገባት ምርጫቸውን ለመጠበቅ፣ የኣጭርና የረጅም ግዚ መፍትሄዎችንና ኣማራጮችን በመዳሰስ ላይ ይገኛሉ።
የኣጭር ግዜ መፍትሄው፣ የክፍለ ሃገሩ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባሳለፈው ውሳኔ ላይ ዳግመ ግምት እንዲያደረግ የሚጠይቅ የክስ እርምጃ መውሰድ ነው። በተጨማሪም፣ calling on ኣገረገዢ ኢንስሊ( Governor Inslee) እና ሌሎች ህግ ኣርቃቂዎች ውሳኔውን በኣስቸካይ እንዲነጋገሩበት ጥሪ እያቀረብን ነው። እያንዳንዱ የህዝባዊ የቻርተር ትምህርት ቤት እንዳይዘጋና ሁሉም ትምህርት ቤቶች ማስተማራቸውን እንዲቀጥሉ ለማድረግ ያሉትን ኣማራጮች ሁሉ እየዳሰስን ነው።

**ጥያቄ፣ ለልጅዎ ትምህርት ቤት ድጋፋቸውን ለመስጠት፣ ወላጆች ምን ማድረግ ይችላሉ?**

እንደ ወላጅ፣ ልጅዎ በህዝባዊ ቻርተር ትምህርት ቤት ውስጥ እንዲማር ለምን እንደመረጡና የቤተሰቦን ግላዊ ታሪክ ለሌሎች ወላጆች ማካፈል ይችላሉ። የቻርተር ትምህርት ቤቶችን ኣድኑ (ሴቭ ደብሊው-ኤ ቻርተር ስኩልስ #SaveWACharter-Schools) በሚባለው ድርጅት መግባት ከፈለጉ፣ ለኣገረገዢ ኢንስሊና ለክፍለሃገሩ ህግ ኣርቃቂዎች ጥሪ በማቅረብ ኣስቸኳይ እርምጃ እንዲወስዱ ማሳሰብ፣ በህዝብ መገናኛዎች ታሪኮን ለሌሎች ማካፈል፣ ለዜና ክፍሎች ደብዳቤ መጻፍና በምን ዓይነት መንገድ ድጋፍ ማድረግ እንደሚችሉ የልጅዎን ትምህርት ቤት መጠየቅ በመሳሰሉ እንቅስቃሴዎች ውስጥ መሳተፍ እንዳለቦት ግምት ውስጥ ኣስገቡ።